


# የኢትዮጵያ ወቅታዊ ችግርና በምሥራቅ

# አፍሪካ ቀጣና የሚኖረው ተፅዕኖ

18 March 2018

**ዘመኑ ተናኘ**

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር ከሚሠሩ አገሮች አንዷ ነች፡፡ በሶማሊያ የመሸገውንና ራሱን ‹‹አልሸባብ›› ብሎ የሚጠራውን ቡድን ከመመከትና ከማዳከም ባሻገር፣ በሱዳንና በደቡብ ሱዳን መካከል ያለውን አለመግባባት ለመፍታት ከላይ ታች ስትል ነበር፡፡ በደቡብ ሱዳን ተፋላሚ ኃይሎች መካከል ያለውን አለመግባባት ለመፍታትም እየሠራች ነው፡፡ በአገሪቱ ያለውን ቀውስ ለመፍታትና በቀድሞው ምክትል ፕሬዚዳንት ሪክ ማቻር (ዶ/ር) እና በፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ማያርዲት መካከል ያለው የፖለቲካ ልዩነት እንዲጠብና ደቡብ ሱዳናውያን ለከፋ ጉዳት እንዳይዳረጉ ከፍተኛ ሚና ስትጫወት መቆየቷን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች አገሪቷ እንደ አገር ነፃነቷን ካወጀች እ.ኤ.አ. 2011 በኋላ በ2015 ነሐሴ ወር ላይ በአዲስ አበባ ውይይት እንዲያደርጉና ልዩነታቸውን እንዲያጠቡ የተጫወተችው ሚናም ከፍተኛ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የደቡብ ሱዳን ቀውስ እንዲረግብና በቀጣናው ሰላም እንዲረጋገጥ በምሥራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አማካይነት ጉልህ ሚና ተጫውታለች፡፡ እየተጫወተችም ትገኛለች፡፡ የሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች ድርድር አስፈላጊነት ላይ ከአፍሪካ አገሮች አልፎ አውሮፓውያንና አሜሪካዊያን ፅኑ እምነት እንዲኖራቸው ከፍተኛ ሥራ እያከናወነች መሆኗ ይነገራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሁለቱ ሱዳኖች መካከል የከፋ የደም መፋሰስ እንዳይከሰት በሚወዛገቡበትና አብዬ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የራሷን ሰላም አስከባሪ ኃይል አሰማርታ ትገኛለች፡፡

ኢትዮጵያ ከሁለቱ ሱዳኖች ባሻገር በሶማሊያ የተረጋጋ መንግሥት እንዲፈጠርና ዜጎች ለችግርና ለከፋ ስቃይ እንዳይዳረጉ ሚናዋ ጉልህ ነው፡፡ በዚያድ ባሬ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ታላቋን ሶማሊያ የመመሥረት ዘመቻ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ሶማሊያ በዚያድ ባሬ ዘመነ መንግሥት ጊዜ በተለይም ታላቋን ሶማሊያ መመሥረት በሚል ዘመቻ ከኢትዮጵያ፣ ከኬንያና ከጂቡቲ ጋር ግጭት ውስጥ ገብታም ነበር፡፡ በተለይ ከኢትዮጵያ ጋር በከፍተኛ ውድመት ያስከተለ ጦርነት አድርጋለች፡፡

ሶማሊያ በአሁኑ ወቅት በገጠማት ፈተና ምክንያት ከግዛት መስፋፋት አባዜ ውስጥ ባትሆንም፣ የተረጋጋችና ከአሸባሪዎች የፀዳች እንድትሆን የኢትዮጵያ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይም እ.ኤ.አ. በ2004 በአገሪቱ የሽግግር

መንግሥት እንዲቋቋም ኢትዮጵያ የበኩሏን ሚና ተጫዋታለች፡፡ በኬንያ ናይሮቢ የተቋቋመው የሶማሊያ የሽግግር መንግሥት የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት በሚባል ቡድን መሰናከል ደርሶበት እንደነበር የሚታወስ ቢሆንም፣ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ እ.ኤ.አ. በ2016 ምርጫ በማካሄድ ፕሬዚዳንት አብዱላሒ መሐመድ ፎርማጆ የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ሆነው ተመርጠዋል፡፡ እ.ኤ.አ. በ2009 በአገሪቱ የተቋቋመውና ራሱን አልሸባብ ብሎ የሚጠራው ጽንፈኛ ቡድን ለሶማሊያ ብሎም ለቀጣናው ከፍተኛ ራስ ምታት ነው፡፡

አልሸባብን ለመዋጋት በሚደረገው ሚና ኢትዮጵያ ቀዳሚውን ሥፍራ እንደምትይዝ ይታወቃል፡፡ ኢትዮጵያ በተመድ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ከፍተኛ ሚና ካላቸው አገሮች አንዷ ነች፡፡ በአሁኑ ወቅት በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ ወታደሮች በአሚሶም ጥላ ሥር ሆነው አልሸባብን በመዋጋት ላይ ይገኛሉ፡፡

አልሸባብ በቀጣናው ባሉ አገሮች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ አሸባሪ ቡድን ነው፡፡ ለአብነትም በኬንያ ውስጥ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና በገበያ ማዕከሎች ባደረሰው ጉዳት የበርካታ ዜጎችን ሕይወት ቀጥፏል፡፡ አሸባሪ ቡድኑ ከኤርትራ መንግሥት ጋር ቁርኝት እንዳለው የተመድ አጣሪ ቡድን አስታውቋል፡፡ ኤርትራ ቡድኑን የጦር መሣሪያ በማስታጠቅና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ እገዛ እንደምታደርግና ቀጣናውን የአሸባሪዎች መናኸሪያ እንዲሆን ትሠራለች ሲል በተደጋጋሚ ጊዜ ባወጣው ሪፖርት ጠቁሟል፡፡

በሌላ በኩል በኢትዮጵያና በኤርትራ መንግሥታት የፖለቲካ ልዩነት ሳቢያ ቡድኑ ለኢትዮጵያ የራስ ምታት ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ምንም እንኳ ኢትዮጵያ በአፍሪካ በተለይም በምሥራቅ አፍሪካ ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች እንደሆነ ቢታወቅም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገር ውስጥ ከፍተኛ ቀውስ ተፈጥሯል፡፡ በአገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች አለመረጋጋቶች ይታያሉ፡፡ ዜጎች ከመኖሪያ ቀዩአቸው ከመፈናቀላቸው በተጨማሪ፣ የሕይወት መጥፋትና የአካል ጉዳት እየደረሰ ነው፡፡ በብዙ አካባቢዎች የዜጎች በሰላም ወጥቶ የመግባት እንቅስቃሴ ሲገደብ ተስተውሏል፡፡ ከፍተኛ ሀብት የወጣባቸው ትልልቅ ፋብሪካዎችና መሠረት ልማቶች በሴኮንድ ወደ አመድነት ተቀይረዋል፡፡ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረገው የሸቀጦች ዝውውር ተስተጓጉሏል፡፡ መንግሥትም አገሪቱን በመደበኛው የሕግ ማስከበር ሥርዓት ማስተዳደር የማይችልበት ጊዜ ላይ መድረሱን አስታውቋል፡፡

በአገሪቱ ያጋጠመውን ቀውስ ተከትሎም በመላ አገሪቱ ተግባራዊ የሚሆን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጇል፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከታወጀ በኋላም ቢሆን የዜጎች ሕይወት ጠፍቷል፡፡ ንብረት ወድሟል፡፡ የዜጎች የመንቀሳቀስ መብት ተገትቷል፡፡

ኢትዮጵያ በሰላም ማስከበሩ ረገድ ከሶማሊያ እስከ ደቡብ ሱዳን፣ ከዋናዋ ሱዳን እስከ ላይቤሪያ፣ ቡሩንዲና ሌሎች አገሮች የተጫወተችው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ቢታወቅም አሁን ግን በአገሪቱ ከፍተኛ ቀውስ አጋጥሟል፡፡

የጂኦ ፖለቲካ ተንታኙ አቶ ልዑልሰገድ ግርማ በኢትዮጵያ የተፈጠረው ችግር ጉዳቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለቀጣናውም እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

የጂኦ ፖለቲካ ተንታኙ ያዕቆብ ኃይለ ማርያም (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ አሁን በኢትዮጵያ የተፈጠረው ችግር ተፅዕኖው በአፍሪካ ቀጣና ጭምር እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ዶ/ር ያዕቆብ አሁን በኢትዮጵያ እየተፈጠረ ያለው ቀውስ በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ ጠቁመው፣ ‹‹ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የምትጫወተው ሰላም የማስከበር ሒደት ጥሩ ቢሆንም፣ በዋናነት ማተኮር ያለባት ግን በውስጣዊ ጉዳይዋ ላይ ነው፤›› ብለዋል፡፡

አገሪቱ አሥጊ ደረጃ ላይ እንዳለች የጠቆሙት ዶ/ር ያዕቆብ፣ አሁንም ሚናዋን በአገር ውስጥ ጉዳይ ማድረግ እንዳለባት አሳስበዋል፡፡

የጂኦ ፖለቲካ ተንታኙ አቶ ዳደ ደስታ ደግሞ ኢትዮጵያ ‹‹የክርስቲያን ደሴት›› እየተባለች ትጠራ እንደነበር አስታውሰው፣ አሁን ደግሞ የሰላም ደሴት የሚል ስያሜ እንደተሰጣት ጠቁመዋል፡፡ ‹‹ረዥም ታሪክ ያላት ከመሆኗ

ባሻገር አካባቢውን እንደ ንስር ይዛው ልትነሳ የምትችል ግዙፍ አገር ነች፤›› ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ ተሰሚነትና ኃያልነት ያላት አገር መሆኗን ያስታወሱት አቶ ዳደ፣ አሁን በአገሪቱ በሚታዩ ችግሮች ሳቢያ ሥጋት መፈጠሩን ጠቁመዋል፡፡

‹‹አካባቢው መረጋጋት የማይታይበትና ለብዙ ጊዜ ሳይፈቱ የቆዩ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡ ደቡብ ሱዳን ያለው ብጥብጥ፣ በሱዳን ያለው አለመረጋጋት፣ የኤርትራና የግብፅ በቀጣናው ያላቸው የመከበብ ዝንባሌ፣ በቀይ ባህር አካባቢ የዓረብ ባህረ ሰላጤ አገሮች የጦር ቀጣና ለመመሥረት ያለው አባዜና ሌሎች ጉዳዮች ተደማምረው አካባቢው በውጥረት የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል፤›› ሲሉ አቶ ዳደ አብራርተዋል፡፡ ይኼን ሁሉ ውጥረት በማስተንፈስና ለችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ በመስጠት ረገድ የኢትዮጵያ ሚና ጉልህ እንደሆነ አስታውሰው፣ አሁን በአገሪቱ ውስጥ እየተከሰተ ያለው ችግር ለቀጣናውም አሥጊ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ በሶማሊያና በሶማሌላንድ የተስፋ ምድር ተደርጋ እንደምትቆጠር አቶ ዳደ ተናግረዋል፡፡ በቀጣናው ሠራዊቷን ከማሰማራቷ ባሻገር አጀንዳ በኢጋድ ደረጃ ይዛ የማስታረቅ ሥራ የምታከናውንና የምታስተባብር እንደሆነች አስረድተዋል፡፡ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የሚሰማራው ሰላም አስከባሪ ኃይልም ሕዝባዊነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ጠቁመዋል፡፡ ‹‹ይኼ ሁሉ የአገሪቱ ሚና በውስጥ ችግር ሳቢያ ጥሩ ሳይሆን ሲቀር ጉዳቱ የሚከሰተው በራስ ላይ ነው፤›› ሲሉ አቶ ዳደ አስረድተዋል፡፡

አቶ ልዑልሰገድ አገሪቱ በውስጥ ችግር በምትታመስበት ጊዜ በዓለም አቀፍም ሆነ በአፍሪካ ደረጃ እየፈጠረች የመጣችው የተሰሚነትና የኃያልነት ሚና አብሮ እንደሚሸረሸር ጠቁመዋል፡፡ አገሪቱ ለዚህ ፈተና የበቃችበት ዋነኛው ምክንያትም፣ ከመልካም አስተዳደር ጋር በተያያዘ በተፈጠሩ ችግሮች ሳቢያ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

‹‹እዚህ ለመድረሳችን ምክንያቱ በፊት ከነበረው መንግሥት በተጨማሪ አሁን ያለው መንግሥት ተደራራቢ ችግሮችን በመፍጠሩ ነው፤›› ይላሉ፡፡ ኢትዮጵያዊነትን ከማጎልበት አኳያም የተሠሩ ሥራዎች አነስተኛ እንደሆኑና ብሔር ተኮር ግጭቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በአገሪቱ ይኼን መሰል ችግሮች ሲፈጠሩ የምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ አብሮ እንደሚበጠበጥ ጠቁመዋል፡፡

‹‹ኤርትራ አካባቢውን በበላይነት ለመቆጣጠር ትፈልጋለች፡፡ ይህንን የምታደርገው ደግሞ ኢትዮጵያን ለማዳከም ነው፡፡ ግብፅ ከዓባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ በቀጣናው ኃያል እንዳትሆን ትፈልጋለች፡፡ ከዚህ በፊት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከኢትዮጵያ ጋር ወደ ጦርነት ገብታለች፡፡ ውጤታማ ግን አልነበረችም፤›› ሲሉ ያብራሩት አቶ ልዑልሰገድ፣ በቀጣናው ይኼን መሰል ጂኦ ፖለቲካዊ ቀውስ እያለ የአገር ውስጥን ጉዳይ በአፋጣኝ መፍታት ተገቢ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ሽብርተኝነትን ከመዋጋት ባሻገር ኃያል እየሆነች እንደመጣች የሚናገሩ ወገኖች አሉ፡፡ የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግሥታት ካለፉት አሥርት ዓመታት ወዲህ ግንኙነታቸው እየሻከረ ከመምጣቱ በተጨማሪ ወደ ጦርነት ገብተው እንደነበር ይታወሳል፡፡ ኤርትራ አሸባሪዎችን ትደግፋለች በማለት ኢትዮጵያ ትኮንናለች፡፡ ኤትርትራ በበኩሏ የኢትዮጵያ መንግሥት ተዳክሞ ማየት እንደምትፈልግ አቶ ልዑልሰገድ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል ከዓባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ የግብፅ መንግሥት አገሪቱ ተዳክማ ማየት ይፈልጋል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ አቶ ልዑልሰገድ፣ ‹‹ጅብ በቀደደው ውሻ ይገባል ይባላልና አሁንም ወሳኝ ጊዜ ላይ ነው ያለነው፤›› ይላሉ፡፡ በአገሪቱ የሚታየው ፖለቲካዊ ቀውስ ተባብሶ ሌላ ኪሳራ ሳያደርስና በቀጣናው ትርምስ ሳይፈጠር ችግሩን አሁንም ቢሆን መፍታት እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡ የኢሕአዴግ አመራሮች ስብሰባ ላይ እንዳሉ ያስታወሱት አቶ ልዑልሰገድ፣ ፓርቲው ቀዳዳዎችን ደፍኖ ይመጣል? ወይስ ቀዳዳው ይሰፋል? የሚለው ዋነኛ ጉዳይ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን በአገሪቱ የተከሰተው ችግር ይፈታል የሚል እምነት እንዳላቸው አክለው ገልጸዋል፡፡

አቶ ዳደ በአገሪቱ የተከሰቱ ችግሮች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ሊከፈሉ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡ አንደኛው የአመራር ቀውስ፣ ሁለተኛው የኅብረተሰቡ የለውጥ ፍላጎትና ከዚህ ጋር ተያይዘው በሚመጡ ችግሮች ጋር የተያያዙ የመልካም አስተዳደር፣ የፍትሕና ሌሎች ጉዳዮች፣ ሦስተኛው ደግሞ የሰላምና የደኅንነት ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ችግሮች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡ የእነዚህ ችግሮች ዋነኛ ምንጭ ግን የፖለቲካ አመራሩ ነው ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ የፖለቲካ አመራሩ ሳይስተካከል ችግሮችን መፍታት እንደማይቻል ያስታወሱት አቶ ዳደ፣ ይኼን ክፍተት እንደ መልካም አጋጣሚ በመቁጠር እጃቸውን ለማስገባት የሚፈልጉ ኃይሎች እንዳሉም ገልጸዋል፡፡ ‹‹ምንም ተስፋ ያለው አገር አይደለም ብለው የሚያስቡ፣ በአገሪቱ ብሎም በቀጣናው ቀውስ ለመፍጠር የሚታትሩ ኃይሎች አሉ፤›› ብለው፡፡ ‹‹እንኳን እንደዚህ ተዝረክርከህ ቀርቶ ተጠንቅቀህ እንኳን የማታመልጣቸው አቅም ያላቸው ኃይሎች አሉ፡፡ ይኼን አጋጣሚ ሲያገኙ ትንሹም ትልቁም ይጠቀምብሃል፡፡ ስለዚህ ዋናው ተጎጂ እኛ እንሆናለን፡፡ የሚያንዣብቡ ጅቦች አሞራዎች አሉ፡፡ እነሱ ያባብሱታል፡፡ አሁን ባለው ብጥብጥ እንኳ ብዙ ብሮችና እጆች ገብተውበታል፤›› ብለዋል፡፡

‹‹ይኼ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው የነበረህን መልካም ስምና ተፅዕኖ ታጣለህ፡፡ ብርሃን መስጠት የምትችል አገር እንዲህ ዓይነት ችግር ውስጥ ገብታ ራሷን ማላቀቅ ሲያቅታት ማየት ከባድ ነው የሚሆነው፤›› ሲሉ አቶ ዳደ አስረድተዋል፡፡

ኢትዮጵያ አሁን ችግር ውስጥ ብትሆንም ከዚህ ችግር መውጣትና ወደ ቀድሞ ኃያልነቷና ተሰሚነቷ መመለስ አይሳናትም ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ፡፡ ዶ/ር ያዕቆብ በአገሪቱ በርካታ ችግሮች ሲከሰቱ ቢስተዋልም መፍታትና ከገባችበት ቀውስ ማውጣት እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡ ዋናው የመፍትሔ አካልም በአገሪቱ የውስጥ ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ሁሉ ችግር የመውጫ መንገዱ ግን አንድ ብቻ እንደሆነም አክለዋል፡፡ እሱም ገዥው ፓርቲ ሥልጣኑን ለሕዝብ አስረክቦ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡ ‹‹ከዚህ ውጪ የሚታየኝ ነገር የለም፡፡ ለውጡ መሠረታዊ መሆን አለበት፡፡ የሽግግር መንግሥት ተቋቁሞ ሕዝቡ በፈለገው መንገድ ብሔራዊ ዕርቅ እንዲወርድ ሊሠራ ይገባል፡፡ የሕዝቡን ክፍፍል መጠገን ያስፈልጋል፡፡ ይኼን እስካላደረግን ድረስ ጠላትን ልንቋቋም አንችልም፤›› ሲሉ ዶ/ር ያዕቆብ አብራርተዋል፡፡

አቶ ልዑልሰገድ በበኩላቸው በአገሪቱ የተፈጠረው ቀውስ ዋነኛ ማጠንጠኛው ከሥልጣን ባለቤትነት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ‹‹ኢትዮጵያን የሚመራት ከየትኛው ደም ነው? የሚለው ነው አሁን እያበጣበጠን ያለው፡፡ ከዚህ በፊትም በታሪክ ስንበጣበጥ ነው የኖርነው፡፡ ስለዚህ መፍትሔው ይኼን ታሪክ መለወጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያን የሚመራው ማን ነው? ሲባል ኢትዮጵያዊ ብቻ ነው መባል ያለበት፡፡ የዘረኝነት አስተሳሰባችንን መተው አለብን፡፡ ኢትዮጵያዊነት የሚዳብርበትና ኢትዮጵያዊነት ብቻ የሚቀነቀንበት ጊዜ መፈጠር አለበት፡፡ ይኼ ችግር ከገዥው ፓርቲ ነው ጎልቶ የወጣው፤›› ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ሁለተኛው መፍትሔ ብለው የጠቆሙት ደግሞ አገሪቱን ከገጠማት ፈተና ተነስቶ፣ ችግሮችን በመለየትና መፍትሔ በማስቀመጥ መፍታት እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡

አቶ ዳደ ለችግሩ መፍትሔ መሰጠት የነበረበት ከዚህ በፊት እንደነበር አስታውሰው፣ ‹‹ቀውስ ውስጥ ያለ አመራር ከቀውስ መውጣት ይችላል ወይ? አቅሙስ አለው ወይ? ብለን ብንጠይቅ መልሱ ይቻላል ነው፤›› ብለዋል፡፡

‹‹አመራሩ በተዝናናና በተዝረከረከ ሁኔታ ውስጥ ቢቆይም አዝማሚያውን ዓይቶ ማስተካከያዎች ማድረግ ይችላል፡፡ ዋናው ማስተካከያ መምጣት ያለበት ከራስ ብቻ ሳይሆን ከሕዝቡ ጋር በመሆን ነው፤›› በማለት ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ በተለይም ካለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ወዲህ ከራሷ አልፋ በደቡብ ሱዳን፣ በሶማሊያ፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲና በላይቤሪያ የሰላም ማስከበር ሚና ተጫውታለች፡፡ አሸባሪነትን በመዋጋት በተለይም በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ከፍተኛ ቀውስ እያደረሰ ያለውንና አልሸባብ ተብሎ የሚጠራውን ቡድን በመከላከልና በማዳከም ረገድ ሚናዋ

ከፍተኛ ነው፡፡ በአፍሪካ ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይም ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር ከማድረግ አኳያ ሚናዋ ጉልህ እንደሆነ ቢታወቅም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቀውስ ውስጥ ገብታለች፡፡ በቀውሱ ሳቢያም በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ችግር ተፈጥሯል፡፡ አገሪቱ በመደበኛው የሕግ ማስከበር ሥርዓት ወጥታ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንድትተዳደር ተደርጓል፡፡

ኢሕአዴግ በአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታና በፓርቲው የውስጥ ችግር ላይ መምከር ከጀመረ አንድ ሳምንት ሊሞላው ነው፡፡ የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዋነኛ የመወያያ አጀንዳ በትክክል ምን እንደሆነ ባይታወቅም፣ በአገሪቱ በተለይም በኦሮሚያ ክልል እየተፈጠረ ባለው የፀጥታ ችግር ላይ ሰፊ ሽፋን በመስጠት እየተወያየ እንደሆነ ይነገራል፡፡

የሥራ አስፈጻሚው ስብሰባ በቅርብ ቀን እንደሚጠናቀቅና የብሔራዊ ምክር ቤት ስብሰባ በሚቀጥለው ሳምንት እንደሚካሄድ የኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ከሰጡት መግለጫ ለማወቅ ተችሏል፡፡ አገሪቱ በበርካታ ችግሮች ተተብትባ ባለችበት ወቅት፣ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ይሆናል? ተተኪው ጠቅላይ ሚኒስትርስ በአገሪቱ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ ያደርጋል? የሚሉ ጥያቄዎች አሁንም ምላሽ ያላገኙና በብዙ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ መነጋገሪያ ናቸው፡፡